(/) የት ነው የሚሸምቱት? አሜሪካ

# እንኳን ወደ ሸማች ማዕከል በደህና መጡ።

እንዴት ልንረዳዎ እንችላለን?

## የ Shopper መተግበሪያ አጠቃቀም መመሪያዎች

Shipt የ Shipt መድረክን በመጠቀም ለሚያደርሱ (“ሸማቾች”) ቁምነገር ያላቸው ዕድሎችን ለማቅረብ ቁርጠኛ ነው። Shipt የንግድ ስራቸዉን ለማሳደግ፣ ደንበኞች የሚጠብቁትን ለማሟላት እና ለማለፍ እንዲሁም ሕጋዊ መስፈርቶች ለማክበር ከሚጓጉ ሸማቾች ጋር በመተባበሩ ኩራት ይሰማዋል።

ሸማቾች እና ደንበኞች የ Shipt ን መድረክ ሲጠቀሙ በሙያ ሥነ ምግባር የተሞላ ተሞክሮ እንዲኖራቸው እና ደኅንነት እንዲሰማቸው እነዚህን የ Shopper መተግበሪያ አጠቃቀም መመሪያዎች (“መመሪያዎች”) ፈጥረናል። እነዚህን መመሪያዎች አለማክበር የ shipt ን የሸማች ስምምነት የሚጥስ በመሆኑ ሸማች ከ shipt መድረክ እንዲወገዱ ሊያደርግ ይችላል። Shipt ማስወገዱን ተገቢ መሆኑ ከመወሰኑ

በፊት ጉዳዩ መመርመር ሊያስፈልገዉ ይችላል። ምርመራ በሚካሄድበት ጊዜ የሸማች መለያ ሊታገድ ይችላል። ስለማስወገድ የበለጠ መረጃ ለማግኘት እዚህ ይጫኑ (https://www.shipt.com/shopper/deactivations)።

## የ Shipt ማህበረሰብን ማክበር እና ደኅንነት መጠበቅ

Shipt በሸማቾች፣ በደንበኞች፣ በዋና መሥሪያ ቤት ሰራተኞች፣ እና በችርቻሮ አጋሮች መካከል ለተፈጠረዉ አስደናቂ ማህበረሰብ ትልቅ ቦታ ይሰጣል።
ባለ 5-ኮከብ ተሞክሮ ለማቅረብ ሁሉ ጊዜ ድጋፍ እንዲሰማዎት ለማረጋገጥ የምንሠራ ሲሆን፣ በተጨማሪም ይህ አስፈላጊ የግንኙነት ምህዳር እንዲበለፅግ የበኩላችሁ አስተዋጽኦ እንድታደርጉ እንጠብቃለን።

ማህበረሰባችን በመጠበቅ ረገድ ልትጫወቱት የምትችሉት ሚና የሚከተሉት ናቸው፦

- ደንበኞች፣ የችርቻሮ አጋሮች፣ የመደብር ሰራተኞች፣ የዋና መሥሪያ ቤት ሰራተኞች፣ እና ሌሎች ሸማቾችን በአክብሮት መያዝ፤
- በሙያ ሥነ ምግባር በተሞላ መንገድ ከሸማቾች፣ ከደንበኞች፣ ከመደብር ሰራተኞች፣ እና ከዋና መሥሪያ ቤት ድጋፍ ሰጪዎች ጋር መስተጋብር መፍጠር፤
- የደንበኞች እና የሌሎች ሸማቾች ግላዊነትን ማክበር። ይህ ደንበኞች እና ሸማቾችን ያልተፈቀዱ ፎቶግራፎች ከማንሳት መቆጠብ፣ የሌሎች የግል ጉዳዮችን ግምት ወስጥ ማስገባት፣ እና ጉልበተኛነት ወይም ትንኮሳ ተደርጎ ሊወሰድ ከሚችል ባህሪ መቆጠብን ይጨምራል፤
- ጭፍን ጥላቻ የሚንፀባረቅበት አነጋገር ወይም እንደ መድልዎ ሊቆጠሩ የሚችሉ አስተያየቶች ከመጠቀም መቆጠብ፤ እና
- ለልዩ የአመጋገብ ገደቦች እና ምርጫዎች የሌሎችን ስሜት መረዳት ይለማመዱ።

በ Shipt ደኅንነት ቅድሚያ የሚሰጠዉ ጉዳይ ነው። ስለዚህ፣ ደንበኞቻችን፣ የችርቻሮ አጋሮች፣ ሰፊው ህዝብ፣ የዋና መሥሪያ ቤት ሰራተኞች፣ እና ሌሎች ሸማቾች የደኅንነት ስጋት ወይም አደጋ ላይ የሚጥል ማንኛውንም ባህሪ ካሳዩ ለመወገድ ምክንያት ሊሆን ይችላል። እነዚህ የሚከተሉት ያካትታሉ፣ ነገር ግን በዚህ አይወሰኑም፦

- ዓመፅ ወይም ተገቢ ያልሆነ ባህሪን ጨምሮ ነገር ግን በዚህ አይወሰኑም፤
    - ጥቃት እና/ወይም ብጥብጥ መፈጸም ወይም ለመፈጸም ማስፈራራት፤

- በአካላዊ ወይም በኤሌክትሮኒክ መሣሪያ ጠበኛ የሆኑ ምልክቶችን መጠቀም፤
- አእምሮ የሚጎዳ ማስፈራሪያ ወይ ባህሪ ላይ መሳተፍ፤
- ደንበኞችን ስለ ክፍያ ወይም ደረጃ አሰጣጥ ወይም ስለ ጉርሻ ማስጨነቅ፤
- ተገቢ ያልሆነ ቋንቋ ወይም ጸያፍ ቃላትን በመጠቀም መነጋገር፤
- አገልግሎቶች ከሰጡ በኋላ ያለ ደንበኛው ፍቃድ ወደ ደንበኛዉ ቤት መግባት ወይም መመለስ፤ እና/ወይም
- ሌሎች የ shipt አባላትን በተመለከተ ሆን ብሎ የሐሰት ክስ ማቅረብ፤

- ደንበኞች ወይም ሌሎች ሸማቾችን ያልተፈለጉ የግል ጥያቄዎች መጠየቅን ጨምሮ ያልተፈለገ ግንኙነት ማድረግ፤
- ስለ ደንበኞች ወይም ሌሎች ሸማቾች ያለፍቃድ የግል መረጃ ይፋ ማድረግ፤
- በ Shipt መድረክ አገልግሎቶች በሚያቀርቡበት ጊዜ ህገወጥ አደንዛዥ እፆችን ወይም አልኮል መጠቀም ወይም ተጽዕኖ ሥር መሆን፤
  - በካሊፎርኒያ፦ በ shipt መድረክ ላይ አገልግሎቶች በሚያቀርቡበት ጊዜ በአደንዛዥ ዕፅ ወይም በአልኮል ተጽዕና ስር ናቸው ተብለው ለሚጠረጠሩ ማንኛውም ሸማቾች shipt ተጨማሪ ምርመራ እስከሚያደረግ ድረስ ለ shipt መድረክ ያላቸው ተደራሽነት ይታገዳል፤
- የክልሉ ህግ ይህን ገደብ በግልጽ ካልከለከለው በስተቀር የሦስተኛ ወገን ቸርቻሪ ንብረት ወይም የደንበኛ ቦታ ላይ ነፍጥ ወይም የጦር መሣሪያ ይዞ መገኘት፤
- በ Shipt መድረክ አገልግሎቶች በሚያቀርቡበት ጊዜ በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ፤
- ተንኳሽ ወይም አድልዎ አድራጊ የሆነ ባህሪ ለምሳሌ አጸያፊ ምልክቶች፣ ስድብ ወይም ሌሎች አላስፈላጊ ድርጊቶች መፈጸም። shipt በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ በዘር ሃረግ፣ በትውልድ ሃገር፣ በሃይማኖት፣ በእምነት፣ በእድሜ፣ በአካላዊ ወይም የአእምሮአዊ አካል ጉዳት፣ በጾታ፣ በሥርዓተ ፆታ፣ በወሲባዊ ዝንባሌ፣ በጾታ ማንንነት ወይም መገለጫ፣ በጤና ሁኔታ፣ በዘረ መል መረጃ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ ወይም በወታደራዊ ወይም የቀድሞ ወታደራዊ ሁኔታ የሚደረግ መድልዎ ወይም ትንኮሳን አይታገሰም። የ Shipt's ወሲባዊ ትንኮሳ መከላከያ ፖሊሲ እዚህ ይገኛል (/ትንኮሳ-መከላከያ-ፖሊሲ)፤
- በ Shipt መድረክ ጥንቃቄ በጎደለዉ ወይም ደኅንነቱ ባልተጠበቀ መንገድ ማሽከርከር፤
- እንደ በማሽጊያ መነካካት፣ ለሽያጭ ያልተዘጋጁ እቃዎች ቦርሳ ላይ ማስቀመጥ፣ ሙቀት ተቆጣጣሪ ቦርሳዎችን ማምጣት ወይም መጠቀም አለመቻል፣ እቃዎች ለማጓጓዝ ንጹህ መኪና መያዝ አለመቻል ወይም የደንበኞች እቃዎች በጭስ የተበከሉ ማድረግ ያለ የምግብ ደኅንነትን አደጋ ላይ የሚጥል ድርጊት መፈጸም፤

- እንደ ሸማች ተቀባይነት ካላገኘ እና ከእርሰዎ ጋር ለመሸመት ወይም ለማድረስ ካልተፈቀደለት ሌላ ግለሰብ ጋር በ Shipt መድረክ አገልግሎቶች መሰጠት፤ እና/ወይም
- ከሚመለከታቸው ህጎች ጋር የሚስማማ የመጀመሪያ ወይም ቀጣይ የወንጀል ዳራ ፍተሻ እና/ወይም የሞተር ተሽከርካሪ ሪፖርት ፍተሻ ማለፍ አለመቻል።

የ Shipt መድረክ በሚጠቀሙበት ጊዜ የእርሰዎን ደኅንነት መጠራጠር ከጀመሩ 24/7 ደረጃ-በ-ደረጃ እርዳታ ለማግኘት የ shipt ን የድጋፍ ቡድን ያነጋግሩ። በተጨማሪ ታታሪው የ Shipt እምነት እና ደኅንነት ቡድናችን አስጊ ሊሆኑ የሚችሉ ባህሪያትን የሚመለከቱ ሪፖርቶችን በሙሉ ይገመግማል። ሸማችን እንዴት እንደምንጠብቅ እዚህ የበለጠ ይወቁ (https://www.shipt.com/shopper-safety/).

## የማህኅበራዊ ሚድያ ማህበረሰብ

እንደ ሸማች Shipt ይፋዊ የፌስቡክ የሸማች ሳሎንን እንዲቀላቀሉ እርስዎን ይጋብዝዎታል። ይህ የመሰመር ላይ ቡድን ሸማቾች እንደ ማህበረሰብ አንድ ላይ የሚሰባሰቡበት ቦታ ሲሆን፣ ሙያዊነቱን ጠብቆ እንዲቆይ ቡድኑ በ shift ይተዳደራል። ወደ ሳሎን የሚቀላቀሉ ሸማቾች ሊከተሏቸው የሚገቡ መመሪያዎችን እና የሚጠበቁባቸውን ነገሮች የያዘን ዝርዝር በሸማቾች ሳሎን "ፋይሎች" ክፍል ውስጥ (እና በፌስቡክ ቡድን "ደንቦች" ክፍል ውስጥ) ማግኘት ይችላሉ።

## የአገልግሎት ደረጃዎች

የ shipt ን መድረክ የሚጠቀሙ ደንበኞች ልምዱ በተቻለ መጠን ግላዊ እና የማይረሳ እንዲሆን ይጠብቃሉ። የአገልግሎት ደረጃዎች ሲከበሩ ደንበኞች ተጨማሪ ትዕዛዞች እንዲያደርጉ የሚበረታቱ ሲሆን፣ ይህ ደግሞ ለሸማቾች በ shipt መድረክ ላይ የበለጠ ገንዘብ የማግኘት እና የንግድ ሥራቸው የማሳደግ እድል ይሰጣቸዋል። በዚህ ምክንያት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የአገልግሎት መስፈርቶች ማሟላት አለመቻል የ shipt መድረክን አለመረጋጋት ያስከትላል እና ለመታገድ ምክንያት ይሆናል፦

- ቢያንስ 4.7 የደንበኛ ደረጃ መጠበቅ አለመቻል፤

- ለሸመታ እና የማድረስ ትዕዛዞች እና የማድረስ ብቻ ትዕዛዞች ቢያንስ የ90 በመቶ የሰዓት አክባሪነት መቶኛ ማቆየት አለመቻል፤
- ዝቅተኛ የሆነውን 90 በመቶ የአስተማማኝነት ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ደረጃ ይዞ መቆየት አለመቻል፤
- ለመዘግየት ይቅርታ የሚሰጡ ትዕዛዞች ጨምሮ ከመጠን በላይ ትዕዛዞች መቀበል እና በተጠየቀው የመላኪያ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ማጠናቀቅ አለመቻል፤
- በተደጋጋሚ በአንድ መንገድ ላይ ያሉትን ጥቅሎች በሙሉ ማንሳት አለመቻል፤
- በተደጋጋሚ ወደ ቸርቻሪው ወይም መዳቢው ማዕከል አርፍዶ መድረስ፤
- በተደጋጋሚ በማንሻ የጊዜ ሰሌዳው 60 ደቂቃዎች ውስጥ ያሉ መስመሮች መተው፤
- በተደጋጋሚ ዘግይተው የሚጠናቀቁ መሰመሮች፤
- በተደጋጋሚ ጥቅሎችን እና/ወይም እቃዎችን በተገቢው የመላኪያ አድርሻ አለማደረስ፤
- በተደጋጋሚ የተሳሳቱ፣ የጎደሉ፣ ወይም የተጎዱ እቃዎች በትዕዛዝ ላይ ማድረስ፤
- በተደጋጋሚ ጥቅሎችን ለማድረስ ሳይሞክሩ መመለስ፤
- ያለ በቂ ምክንያት በተደጋጋሚ የተጠየቀው ትዕዛዝ ማጠናቀቅ አለመቻል፤
- በተደጋጋሚ የተመላሽነት ማረጋገጫ ፎቶግራፎችን በማስረጃ ማቅረብ አለመቻል እና/ወይም የ Best Buy ጥቅሎችን ወደ መደብር ሲመልሱ ጥቅሉን እና ዙሪያውን በግልጽ የሚያሳዩ ፎቶግራፎችን በማስረጃ ማቅረብ አለመቻል፤
- በተሳሳተ መንገድ የዕቃ መረጃን ወደ Shopper መተግበሪያ ማስገባት፣ የተሳሳቱ ተተኪዎችን ማካተት፣ ለደንበኛ የተገዙ እቃዎችን ያልተገኙ ብሎ ምልክት ማድረግ ወይም ለተሳሳተ ደንበኛ እቃ ማድረስ፤
- አንድ መደብር/ቸርቻሪ ያወጣዉን የመደብር/ቸርቻሪ ፖሊሲዎች/መመሪያዎች መከተል አለመቻል። አንድ የችርቻሮ አጋር አንድ ሸማች ወደ ሱቁ እንዳይገባ የተከለከለ መሆኑን የሚያሳይ ሰነድ ካቀረበ፣ ይህ ሁኔታ ሸማቹ ከዚህ የችርቻሮ አጋር ጋር የተያያዙ ሥራዎችን መቀበል እንዳይችል ሊያደርግ ይችላል፤
- በሸማች ማዕከሉ እንደተገለጸው የተከለከሉ እቃዎችን ማድረስ (/building-your-business/prohibited-items)፤
- ደኅንነቱ ያልተጠበቀ ወይም በሌላ መልኩ ተገቢ ያልሆነ ባህሪን የሚመለከቱ ሪፖርቶችን መቀበል፤
- ደንበኞች ማነጋገር አለመቻል ወይም በተጠየቀው የመላኪያ የጊዜ ሰሌዳ በ30 ደቂቃዎች ውስጥ መሸመት አለመጀመር፤ እና/ወይም
- ተደጋጋሚ እና ስልታዊ በሆነ መንገድ ትዕዛዞች መልሶ ለማግኘት እያሰቡ መልቀቅ።

## መድረኩን አላግባብ መጠቀም

ደንበኞች እንደ ምግብ፣ የቤት እቃዎች እና ሌሎች እቃዎች ያሉ ሸቀጦችን ወደ ቤታቸው እና ወደ ንግድ ቦታቸው ለማድረስ በሸማቾች ላይ የሚገርም እምነት ይጥላሉ። በመሆኑም ሸማቾች በታማኝነት እና በሃቀኝነት እንዲሸምቱ እና እንዲያደርሱ ይጠበቃሉ። ይህንን የመተማመን ስሜት በማጭበርበር፣ በአለመታመን ወይም በማታለል መጣስን መታገስ አይቻልም።

ከሚከተሉት በአንዱ ድርጊት ላይ መሳተፍ መወገድን ሊያስከትል ይችላል፦

- በደንበኛው የ shipt ትዕዛዝ ላይ አስፈላጊ ከሆኑት እና ከተጠየቁት እቃዎች ውጪ የሆነን ሌላ ማንኛውም ነገር መግዛት፤
- ደንበኛው የጠየቃቸውን ዕቃዎች ለመግዛት በመደብሩ ውስጥ ከመክፈል ውጭ ለሆነ ዓላማ የ shipt ን ካርድ መጠቀም፤
- በተመሳሳይ ስምም ሆነ በቅጽል ስም ከአንድ በላይ የሸማች መለያዎችን መያዝ፤
- ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ጨምሮ ሌሎች ያልተፈቀደላቸው ግለሰቦች በእርስዎ የሸማች መለያ አገልግሎቶች እንዲያጠናቅቁ ማጋራት ወይም መፍቀድ፤
- በችርቻሮ ነጋዴው የተከለከለ በሆነበት እያንዳንዱ ጉዳይ ላይ የ shipt ን የሽልማቶች ካርድ ለግል ጥቅም መጠቀም ወይም ነጥቦች ለማግኘት ለ Shipt ትዕዛዞች የግል ሽልማቶችን መጠቀም፤
- የሪፈራል ቦነስ ፕሮግራም፣ የሸማች ጉርሻዎች ወይም ሌሎች የ Shipt ማስተዋወቂያዎች ወይም ማበረታቻዎችን አላግባብ መጠቀም ወይም ማጭበርበር፤
- ልዩ ደመወዝ ለመቀበል እና/ወይም ለመጨመር በማሰብ ትዕዛዙን ለመሰረዝ ዓልሞ በመተግበሪያው ውስጥ በሐሰተኛ ትዕዛዝ “መሸመት”፤
- ለማድረስ ሳይሞክሩ በማንሳት ላይ ያሉትን የማድረስ ብቻ ትዕዛዝ ጥቅሎች በተደጋጋሚ መሰረዝ፤
- Shipt በማይሰራበት ዚፕ ኮዶች በ Shipt መደረክ ላይ ሥራ ማጠናቀቅ፤
- እንደ iBotta ባሉ የሽልማት መድረኮች ላይ ለግል ጥቅም ከ Shipt ትዕዛዞች የተገኙ የመደብር ደረሰኞችን መጠቀም፤
- የሽልማት ነጥቦች እና ተመላሽ ገንዘብ ለማግኘት በፈቃደኝነት ለ Shipt ትዕዛዞች በግል ካርድ መክፈል፤
- የሚከተሉትን ጨምሮ ነገር ግን በእነሱ ሳይወሰን የደረጃ አሰጣጥ ሥርዓትን ማጭበርበር፦
  - የደንበኛ ትዕዛዝ የማግኘት እድልን ለመጨመር ደንበኛ ለሌሎች ሸማቾች ዝቅተኛ ደረጃ እንዲሰጡ ማበረታታት
  - በእርስዎ የደንበኛ መለያ ወይም በቤተሰብዎ ውስጥ ባለ መለያ የቀረበን ትዕዛዝ መቀበል እና ማድረስ

  - ደንበኞች ባለ 5-ኮከብ ደረጃ እንዲሰጡዎት ያለ አግባብ ጫና ማሳደር፤
- ትዕዛዙን ለማጠናቀቅ የወሰደውን ጊዜ እና የተጓዙትን ርቀት ሆን ብሎ ማዛባት ወይም ማጭበርበር፤
- ትዕዛዙ ሳይደርስ Shopper መተግበሪያ ላይ እንደደረሰ አድርጎ ምልክት ማድረግ፤
- በሸማች ማመልከቻ ሂደት ወቅት ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የሐሰት የግል መለያ መረጃ መስጠትን ጨምሮ ነገር ግን በዚህ ሳይወሰን የሐሰት ስም፣ የትውልድ ቀን ወይም የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር መስጠት ወይም በሌላ መንገድ ሃቀኝነት የጐደለው ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈጸም፤
- ትክክለኛ፣ የተሟላ እና ወቅታዊ የሆነ የሸማች መለያ መረጃ ማቆየት አለመቻል፤
- በመተግበሪያው ውስጥ የተመረጠው ስም ላይ ጸያፍ ቃል መጠቀም እና/ወይም የተመረጠውን ስም ከደንበኞች ጉርሻ ለመጠየቅ መጠቀም፤
- የንግድ ምልክቶች፣ የቅጂ መብቶች ወይም ሌሎች የአዕምሯዊ ንብረት መብቶችን ያለፍቃድ መጠቀም፤
- በደንበኛ ወይም በሸማች መለያ አማካይነት በሸማች የሚደረግ ማንኛውም ሃቀኝነት የጎደለው ወይም የማጭበርበር ተግባር፤ እና/ወይም
- በካሊፎርኒያ፦ በ Shipt መድረክ ላይ ያለማቋረጥ የ6 ሰዓት እረፍት ሳይወስዱ በ24-ሰዓት ውስጥ ከ12 ሰዓታት በላይ መሥራት።

## የሚመለከተው ሕግ ወይም መመሪያ ላይ የሚፈጸም ጥሰት

አንድ ሸማች በ Shipt መድረክ በኩል አገልግሎቶች በሚሰጥበት ጊዜ የፌዴራል፣ የክልል ወይም የአከባቢ፣ መስተዳድርን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የሚጥስ ከሆነ እገዳ ወይም መወገድ ሊያጋጥመው ይችላል። ምሳሌዎቹ የሚከተሉትን ያካትታሉ ነገር ግን በእነዚህ አይወሰኑም፦

በ Shipt መድረክ በኩል አገልግሎቶች በሚያቀርቡበት ጊዜ የሚመለከታቸውን የፌዴራል፣ የክልል ወይም የአካባቢ መስተዳድር ሕጎች፣ ደንቦች ወይም መመሪያዎች አለማክበር፤

ከሚመለከታቸው የሕግ እና/ወይም የውል መስፈርቶች ጋር የሚስማማ በቂ ኢንሹራንስ መያዝ አለመቻል፤

በተፈቀደላቸው አካባቢዎች አልኮል ለማድረስ ፈቃድ ላላቸው ሸማኞች፣ መታወቂያ አለመጠየቅ፣ ለአካለ መጠን ላልደረሰ ወይም በግልጽ ለሰከረ ሰው አልኮል ማድረስ፣ ተገቢ ያልሆነ መታወቂያ መቀበል ወይም አልኮል የሚያካትት እና በአካል የሚቀርብ ተቀባይ የሌለው ትዕዛዝ መፈጸምን ጨምሮ አግባብነት ያላቸውን የአልኮል ሕጎች፣ ደንቦች እና የችርቻሮ ፖሊሲዎችን አለማክበር፤ እና/ወይም

በመድረኩ በኩል የሐኪም ማዘዣ ትዕዛዞች ለማድረስ እውቅና ላላቸው ሸማቾች፣ የሃኪም ማዘዣ ትዕዛዞችን ያለ ቁጥጥር መተው ወይም ሳይደርስ የቀረ የሐኪም ማዘዣ ትዕዛዝን ወደ ቸርቻሪው አለመመለስ የመሳሰሉ የሚመለከታቸውን የሐኪም ማዘዣ ማድረስ ሕጎች እና ደንቦች አለማክበር።

ለመጨረሻ ጊዜ የዘመነው ኦክቶበር **8** ቀን **2024** ዓ.ም

ይህ አርትዖት ረድቶታል**??** 1052

## ተዛማጅ ርዕሶች


[የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19) ዝማኔዎች እና የደህንነት መመሪያዎች።](/covid-19/coronavirus-update-and-safety-guidance)

(/covid-19/coronavirus-update-and-safety-guidance)

[ከመደብሮች ጋር ብቻ የተያያዙ በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎች](/shop-only/shop-only-faq)

(/shop-only/shop-only-faq)

[**2**-ሰዓት ማቅረቢያ መስኮቶች](/2-hour-delivery-window-faqs)

(/2-hour-delivery-window-faqs)

[የመለያ ጥበቃ እና ደህንነት](/app-functionality/keep-your-shipt-account-secure)

(/app-functionality/keep-your-shipt-account-secure)

[በMeijer የምርት ደረጃን መጠቀም](/adrian/using-the-produce-scale-at-meijer)

(/adrian/using-the-produce-scale-at-meijer)

[በ Shipt Summit Seeker ፕሮግራም በኩል ብቸኛ ሽልማቶችን ያግኙ።](/building-your-business/shopper-rewards)

(/building-your-business/shopper-rewards)

## ማካፈል የሚፈልጓቸው ሀሳቦች አሉዎት?

አስተያየት ስጡ

**(https://survey3.medallia.com/?shipt-shopper-hub)**

## የSummit Seeker ሽልማቶችን ማሰስ ይፈልጋሉ?

ሽልማቶች ያስሱ

**(https://shoppers.shipt.com/buildingyour-business/shopper-rewards)**

## አስቸኳይ እርዳታ ያስፈልግዎታል?

እኛን ያነጋግሩ

**(https://www.shipt.com/contact/).**

Shipt

(/?noredirect)

Download on the App Store

https://apps.apple.com/us/app/shipt-shopper-shop-for-pay/id976353472

GET IT ON Google Play

https://play.google.com/store/apps/details?id=com.shipt.shopper&hl=en_US

https://www.facebook.com/shipt/ https://twitter.com/Shipt https://www.instagram.com/shipt/

https://www.pinterest.com/shipt/

© 2024 Shipt, Inc. እና አገልግሎቶቹ በዚህ ጣቢያ ላይ ከችርቻሮ ነጋዴዎች ጋር የተቆራኙ ወይም የተደገፉ አይደሉም።

የአገልግሎት ውሎች (https://www.shipt.com/terms-of-service/) Privacy (https://www.shipt.com/legal/privacy-policy)
CA የግላዊነት መብቶች (https://www.shipt.com/legal/privacy-policy#california) የእርስዎ የግላዊነት ምርጫዎች (https://www.shipt.com/privacy/intake-form)
የWA ጤና ግላዊነት (https://www.shipt.com/legal/privacy-policy#washington)
ፍላጎት-ተኮር ማስታወቂያዎች (https://www.shipt.com/legal/privacy-policy#online-ad-choices)

በ**Helpjuice** የተጎለበተ የእውቀት መሰረት ሶፍትዌር **(https://helpjuice.com/?utm_campaign=customer_kb)**